ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ
**Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity**
efdpu@aol.com www. Finote.org

# ሳምንታዊ ዜና ዘገባ

## (ህዳር 12 ቀን 2002 ዓ. ም.)

በ1997 ዓ/ም አገር አቀፍ ምርጫ ከመካሄዱ ጥቂት ወራት ቀደም ብሎ በአዲስ አበባ ከተማ በተወሰኑ ወረዳዎች መምሪያና ማቀነባበሪያ ጣቢያዎች መሥርቶ ሰላማዊ ሰዎችን በገፍ የፈጀው የተወርዋሪ ጦር በመጪው ምርጫም ተመሳሳይ ግዴታውን ለመወጣት በየወረዳዎች እየሰፈረ መሆኑን ከሥፍራው የነበሩ ምንጮቻችን ከላኩልን ዜና ለማወቅ ተችሏል፡፡ ምንጮቻችን ተዘዋውረው እንደተመለከቱት በቂርቆስ፣ በጉለሌ፣ በአራዳ፣ በልደታና የካ ክፍለ ከተሞች ጣቢያዎቹ መቋቋማቸውንና የፌደራል ፖሊስ የደንብ ልብስ የለበሱ የወያኔ ነፍሰ ገዳዮች ቦታ ቦታቸውን መያዛቸውን ለማረጋገጥ ችለዋል፡፡

ቁጥራቸው ምን ያህል እንደሆነ ባሁኑ ጊዜ ለመለየት ያልተቻለው እነዚህ የፌደራል መንግስት ነፍሰ ገዳዮች ምርጫ 97 ከተጠናቀቀ በሁዋላ ከ200 በላይ ንጹሃን ዜጎችን ሕይወት አጥፍተው፣ ከነዚህ እጥፍ የሆኑትን አቁስለው፣ በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩትን አፍነው ስውርና ለጤና አደገኛ በሆኑ ቦታዎች በእስር የወረወሯቸው መሆኑ ይታወሳል። ያኔ ከታሰሩት ውስጥ እስከዛሬ በእስር የሚማቅቁ እንዳሉም ይታወቃል። እነዚህ ነፍሰ ገዳዮች ዘንድሮም ከጥቅምት ወር መጨረሻ ጀምሮ በተጠቀሱት ወረዳዎች የቀድሞ ማዘዣ ጣቢያዎችን የተቆጣጠሩ ሲሆን ነዋሪው ሕዝብ ከወዲሁ የፍርሀትና የሥጋት ድባብ እንዳጠላበት የታዘቡ መሆናቸውን ምንጮቻችን በዘገባቸው አካተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በወታደራዊ ፒክ አፕ መኪናዎች የታጠቁ ፖሊሶች በከተማዋ ውስጥ በመዘዋወር የተጠናከረ ጥበቃ በማድረግ ላይ መሆናቸው እየተስተዋለ ሲሆን ምርጫው ከመቃረቡ አስቀድሞ በከተማዋ ያሉ የመንግስት ተቃዋሚዎች ወይንም የተቃዋሚ ደጋፊዎች ናቸው የተባሉትን በሙሉ ለማሠር የተወጠነ ደባ እንዳለ ምንጮቻችን ግምታቸውን አስፍረዋል፡፡ በ1997 ዓ/ም በነፍሰ ገዳይነት የተሰማሩት የአግአዚ ክፍለጦር አባላት ሲሆኑ ዘንድሮ ደግሞ የአፈናና የግድያ እንዲሁም የማሰቃየት በቂ ሥልጠና የተሰጣቸው የፌደራል ፖሊሶች እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡

በተያያዘ ዜና የመለሰ ቡድን ከተወሰኑ ድርጅቶች ጋር የሥነ ስርዓት ደምብ ተፈራረምኩ ቢልም በዚህም ሳምንት ቢሆን በየቦታው የተቃዋሚ ድርጅቶች ደጋፊዎች ናችሁ በሚል ማሰርና ማንገላታት መቀጠሉን ለማወቅ ተችሏል። ወደ አዲስ አበባ የመጣ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዝቅተኛ ደረጃ ባለስልጣን ከወያኔ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከስዩም መስፍን ጋር በዚሁ የሰብአዊ መብት ረገጣ ዙሪያ ተነጋገረ የሚል ወሬ ቢናፈስም የወያኔው ባለስልጣን ይህ ሀቅ አለመሆኑንና አሜሪካ ለመለሰ አገዛዝ ድጋፏን እንደምትቀጥል መወሰኗን ገልጧል። የአሜሪካ የኦባማ አስተዳደር በቅርቡ ቀንደኛውን ወያኔ ዳንኤል ወልደዮሐንስን የሚሊኒየም ቻሌንጅ ኮርፖሬሽን ኃላፊ ብሎ መሾሙ ወያኔን ያስደሰተው መሆኑም ከዚህ ተያይዞ የሚጠቀስ ነው። በኢትዮጵያ ቀደም ሲል የታሰሩት ሊፈቱ ቀርቶ ተጨማሪ እስረኛ በየማጎሪያው እየተወረወረ ከመሆኑ ሌላ ለረሃብ ተብሎ የመጣውንም በእርዳታ ወያኔ በአንድ በኩል ጆንያ ቀይሮ ለሽያጭ ከማቅረቡ ሌላ ኢሕዴግን ያልደገፈ እርዳታ አያገኝም በሚል የምግብ እርዳታውን ለፖለቲካ ግቡ ለመጠቀም መጀመሩም ተጋልጧል። በዘመነ ደርግ ወያኔ ተመሳሳይ ስርቆት ሲያካሂድ የሚያውቁት እንግሊዞች የአሁኑን ጉዳይ እናጣራለን በሚል አሹፈዋል። ከዚሁ በተያያዘ ዜና ደግሞ መኢአድ የዚሁ ሰነድ ፈራሚ መሆኑ ብዙ ውዝግብ ያስነሳ ሲሆን በተፈራራሚዎቹ ላይም መድረክ የተባለው ቡድን የሰጠው አሉታዊ ትችት በድርጅቶች መሀል እሰጥ አገባውን አፋፍሞታል። መድረክ ወደ ምርጫው መግባቱ አይቀርም የሚሉ ብዙ ሲሆኑ ለማንኛውም ይህን እነ ስዬ አብርሃና ነጋሶ ጊዳዳ ያሉበት ስብስብ ከመለስ ዜናዊ ጋር ድርድር ይቀጥል ዘንድ የሽማግሌዎች ኮሚቴ የተባለው የፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅ ቡድን ጥረት ጀምሯልም ተብሏል። ለመለስ አገልጋይ የሆነው ፕሮፌሰር መለስን ሁለቴ ካገኘ በኋላ የመድረክ መሪ የተባሉትን ገብሩ አስራትን፣ መሀንዲስ ግዛቸውና በየነ ጴጥሮስን በአላሙዲ ሆቴል በሼራተን መገናኘቱ ተግልጿል። የሰነድ ፊርማው ዋና ተጠቃሚ የወያኔ አገዛዝ ለመሆኑ በአሁኑ  ጊዜ ጊዜ ግልፅ ሆኗል። በፈራሚዎች ድርጅቶች ውስጥና  በእርስ በርሳቸውና በአባላትና ደጋፊ ዘንድ የተፈጠረው ውዝግብ ለመለሰ ቡድን ጠቅሞታል። የወያኔ ቡድን በምርጫው ዙሪያ በፈጠረው ግርግር ዋና ዋና የሀገሪቷን ጥያቄዎች ወደ ጎን ለማድረግ እየሞከረ መሆኑም ተጋልጧል። በሀገሪቱ የወያኔ ቡድን በምርጫው ዙሪያ በፈጠረው ግርግር ዋና ዋና የሀገሪቷን ጥያቄዎች ወደ ጎን ለማድረግ እየሞከረ መሆኑም ተጋልጧል። በሀገሪቷ የገባውን ርሃብ ልክና ስፋት ለመደበቅ ወያኔ አሁንም እየጣረ ነው። የኢትዮጵያን ለም መሬት ሩቡን ለባእዳን በአሳፋሪ ደረጃ አሳልፎ መስጠቱና ሊሰጥ መወሰኑን አሁንም ለሀገር ጠቃሚ ነው በሚል ሊያደናግር እየሞከረ ነው። በጎንደር ለሱዳን የተሰጠውን መሬት በሚመለከት ትንፍሽ የሚለውም የለም። የኑሮ ውድነት አስከፊ ጣሪያ ላይ ቁብ እንዳለ ነው። በጤና መስክም ያለው ሁኔታ የከፋ ነው። በአጭሩ ዛሬ የሀገራችን ለውጥ ፈላጊ ኃይሎችና ሕዝብ ትኩረት የሚስቡ መሰረታዊ ችግሮች በርካታ ሆነው ሳለ ይህንን ትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር ልዩ ሚዛን አልባ  ጉዳዮንችን እያቈጐሸ ነው።

ሰኞ ሕዳር 7ቀን 2002 ዓ/ም የወያኔ /ኢህአዲግ/ ሥራ አስፈጻሚ አጠቃላይ ስብሰባ ማድረጉን የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ያስደመጠ ሲሆን በስብሰባው ላይ የኢህአዴግ ነባር ሥራ አስፈጻሚዎንችና አዳዲስ የወያኔ ሙሽሮች የተሰኙት የትምህርት ሚ/ር፣ የገጠርና የግብርና ልማት ሚ/ር፣ እንዲሁም መንግስታዊ ድርጅቶች በሕግ ሽፋን የወያኔውን ሕገወጥ ተግባር በማስፈጸም የታወቁት አቶ ብርሃኑ አዴሎ፣ የተወካዮች

ምክርቤት አፈጉባኤ  የማዕድንና ኃይል ሚኒስትሩ አቶ አለማየሁ ተገኑ በዚህ ስብሰባ ላይ ከተገኙት መካከል ሲሆኑ ሌሎችም  አዳዳስ የወያኔ ካድሬዎች በስብሰባው ላይ እንደነበሩ ለማወቅ ተችሏል።

በዚህ ስብሰባ ላይ የአምስት ዓመት መሪ ዕቅድ ለማውጣት የሚያስችል መነሻ ሃሳቦች ለውይይት እንደቀረበ የተገለጠ ሲሆን ለመርሃ ግብሩ አለመሳካት እንቅፋት የተባሉትን አስቀድሞ ማስወገድ ቀዳሚ ተግባር መሆኑን ተሰብሳቢዎቹ እንደተስማሙበት በይፋ የተለጸ ሲሆን እንቅፋቶች የሚባሉት ምን ምንን ያካተቱ መሆናቸው ግን የተገለጸ ነገር የለም።

""

---

ወደ 14 ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ ለአደጋ የተጋለጠ መሆኑና ከዚሁ ውስጥ 6.5 ሚሊዮን የሚሆነው ሕዝብ አስቸኳይ ርዳታ እንደሚያስፈልገው በዜና ማስራጫዎች ሲነገር መቆየቱ ይታወሳል። ረሀቡ በበርካታ አካባቢዎች እየተስፋፋ መሄዱን ከተለያየ አካባቢ ከሚወጡ መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡ በአርሲ ነጌሌ ረሀቡ በጣም እየጸና በመሄዱ ሰዎች ከብት እንኳን የማይበላውን አረም እየቀቀሉ መብላት መጀመራቸው እየተነገረ ነው፡፡ በሌሎች አካባቢዎችም ረሃብተኞች ምግብ ፍለጋ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ መጀምራቸው ታውቋል። ኦሮሚያና አማራ ክልሎች እየተባሉ በወያኔ በሚጠሩ  የተለያዩ ዞኖች ውስጥ የተከሰተው የመደበኛ ምግብና የአልሚ ምግቦች እጥረት አሳሳቢ መሆኑን ኬር የሚባለው ድርጅት ሰሞኑን አስታወቋል፡፡ በምሥራቅና በምዕራብ ሐረርጌና በቦረና ዞን፣ እንዲሁም በደቡብ ጎንደር ውስጥ የተከሰተው የምግብ እጥረት ከበልግ ዝናብ እጥረትና ዘግይቶ ከጀመረው የመኸር ዝናብ ጋር ተያያዥነት እንዳለው ድርጅቱ አስታውቋል፡፡

በምሥራቅና በምዕራብ ሐረርጌ ከአምስት ዓመት በታች ያሉ በምግብ እጥረት የተጎዱ ህፃናት ወደ ተመላላሽ የሕክምናና የምገባ ጣቢያዎች የተወሰዱ ሲሆን፣ ቁጥራቸውም ከጊዜ ወደ ጊዜ መጨመሩም ታውቋል፡፡ በጥቅምት ወር መጨረሻ አካባቢ ከሁለቱ ዞኖች 2096 ያህል ሕፃናት የሕክምናና የምገባ አገልገሎት ማግኘታቸው ተጠቅሷል።

የዕርዳታ ሰጭ ድርጅቶች አስቸኳይ ርዳታ የሚያስፈልገውን ሕዝብ ቁጥር ወደ 9 ሚሊዮን ከፍ አድርገው እየገመቱ ባሉበት ወቅት ለህዝብ  ችግርና እልቂት ደንታ የሌው ወያኔ ቁጥሩን ወደ አምስት ሚሊዮን ዝቅ ለማድርግና ችግሩን ቀላል አድርጎ ለማግቸልቸል ሲሞክር ይታያል።  ወደብ ላይ የደረሰ የዕርዳታ ስንዴ ሳይጓጓዝ ብዙ ወራት እንዳስቆጠረ ጅቡቲ ከሚመላለሱ ሾፌሮች መረዳት የተቻለ ከመሆኑም በላይ ወያኔ ለተራበው ህዝብ የመጣውን ስንዴ ባስቸኳይ አንስቶ ከማከፋፍል ይልቅ እራሱ ለሚነግደው ማዳበርያ ቅድሚያ ሲሰጥ መቆይቱ ታውቋል።  በአንዳንድ አካባቢዎችም ከረሀቡ ጎን ኮሌራ መከሰቱንና ችግሩና እልቂቱ መባባሱ የግበረ ሰናይ ድርጅቶችን ያሳሳባቸው መሆኑ ገልጸዋል።

ወያኔ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ በአማካይ ወደ ሰባት ሚሊዮን ሕዝብ በየአመቱ ከውጭ በእርዳታ ሰጭዎች በሚሰጥ የእህል እርዳታ ላይ ጥገኛ ሆኖ የቆየ ነው። የእህል እርዳታውን ወያኔ ለፖለቲካ መጠቀሚያ አድርጎታል፤ ለራሱ ደጋፊዎች የእርዳታ እህሉን እያከፋፈለ ተቃዋሚዎችን እያስራብ ነው የሚለው የተቃዋሚ ኃይሎች ክስ አንዳንድ አገሮችን ያሳሰበ መሆኑ ታውቋል። ለወያኔ ከፍተኛ እርዳታ ከሚሰጡት መካከል የሁለቱ ማለትም የአሜሪካና የእንግሊዝ ተወካዮች በዚህ ሳምንት በተከታታይ በሰጡት መግለጫ ጉዳዩ ያሳሰባቸው መሆኑና በዚህ ጉዳይ ላይ ምርመራና ክትትል ለማድረግ መወሰናቸውን አስታውቀዋል።

ባለፈው ሳምንት ቅዳሜ የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር (ኦብነግ) 626 የመንግሥት ወታደሮች መግደሉንና በኢትዮጵያና ሱማሌ አዋሳኝ የሆኑ ሰባት መንደሮችን በቁጥጥሩ ስር ማዋሉን ለዜና አውታሮች ባስተላልፈው መግለጫ ይፋ ማድረጉና ወያኔም "የፈጠራ" ወሬ ነው በሚል ወሬውን አጣጥሎ እንዲያውም በውጊያው የኦብነግ 245 ታጣቂዎች መግደሉን ማስታወቁ በዚህ ሳምንት የተሰራጨ ዜና ነበር። በሁለቱም በኩል የተሰራጨው ዜና እጅግ የተጋነነ ከመሆኑ በላይ የነበረው ሁኔታ ከዚህ በጣም የተለየ መሆኑን ከዜና ምንጮቻችን ለመረዳት ችለናል። ባለፈው ሳምንት ህዳር 2 ቀን እሮብ በቀብሪ ደሀር ፣ በደሀጋሀቡር፣ በፊቅ የከረረ ጦርነት የተካሄደ መሆኑና በዚሁ ጦርነት ከመንግስት ከ25 እስከ 30 የሚደርሱ ወታደሮች እንደ ተገደሉ ከወታደራዊ ምንጮች ለመረዳት ተችሏል፡፡ በግጭቱ ወቅት በመንገድ ሥራ ላይ የነበሩ ሠራተኞችና ሌሎች በአካባቢዎቹ በተለያየ ሥራ ላይ የነበሩ ንጹሀን ዜጎችም በተባባሪ ጥይት ህይወታቸው እንዳጡ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ሰኞ ህዳር 7 ቀን በሐረርና ባቢሌ መሀል በምትገኘው በጃካታ አማጽያንና የወያኔ የደቡብ ምስራቅ ዕዝ ወታደሮች ውጊያ ገጥመው 80 ያህል ወታደሮች መገደላቸው ታውቋል። በርካታ ወታደሮችም ቆስለው ከህይወት ፋና ሆስፒታል አቅም በላይ በመሆናቸው በሀረር ከተማ በሚገኙ ሆስፒታል ህክምና እየተደረገላቸው ምሆኑን መረዳት ተችሏል። በወያኔ በኩል በሬ ወለደ ወሬው የደራና የተለመደ ቢሆንም ተቃዋሚው ነን የሚሉትም በበኩላቸው እውነቱ ተነግሮ ሳያልቅ ሀሰትን በማሰራጨት ራሳቸውን እያስገመቱ ናቸው። የኦጋዴን ሕዝብ አረብ ነው ብሎ በቅርቡ ለዓለም ያበሰረው የዚያ አካባቢ የሽምቅ ተዋጊ ቡድን ባለፈው ሰሞን ሰባት ቦታዎችን ውጊያ አድርጌ ያዝኩ ማለቱ ሳይበቃ ከ9 መቶ በላይ የወያኔ ወታደሮችችን ገድልኩ ያለው አነጋጋሪ መሆኑ አልቀረም። ወያኔ በጫካ ዘመኑ ገድልኩ ያለው የደርግ ወታደር ብዛት ሲደመር ከደርግ ወታደር ሁሉ ቁጥሩ መብለጡ መሳለቂያ አድርጎት እንደነበር የሚታወስ ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ ግን በኦጋዴን ታጣቂዎችና በወያኔ መሃል ወጊያ መቀጠሉ የሚታወቅ ነው።

በኦጋዴን ያለው ሁኔታ መባባሱ ወያኔ ከሻዕቢያ ጋር ካለው የሻከረ ግንኙነትም ጋር የተያያዘ መሆኑ ይበልጥ ግልጽ እየሆነ ነው። ሻዕቢያ ለሶማሊያ አማጽያን ወታደራዊ እርዳታ ይሰጣል በሚል በተባበሩት መንግስታት ደረጃም ማዕቀብ ሊደረግበት ሙከራዎች ያሉ ሲሆን በተጨባጭ ግን ሻዕቢያ በቀጥታም ሆነ በሶማሊያ አማጽያን በኩል ለኦጋዴን አማፅያን እርዳታ መስጠቱ ድብቅ አይደለም። በየመን ላለው የሁቲዎች አመጽ ኢራን እርዳታዋን በኤርትራ በኩል ትሰጣለች በመባሉም የመንና ሳውዲ አረቢያ የሻዕቢያን ተቃዋሚዎች ሊረዱ ተነስተዋል የሚለውም ዜና በመናፈስ ላይ ነው። ጂቡቲም ብትሆን ፍሩድ

ለሚባለውና በካዳሚ መሀመድ የሚመራውን አማጽያን ቡድን በመሳሪያ እየረዳ ነው ብሎ በመክሰስ ከውያኔ ጋር ጠበቅ ያለ ወታደራዊ ግንኙነትን እየመሰረተ ነው የሚል ዜናም ተድምጧል። እየተባባሰ ባለው የአካባቢ ቀውስ ደቡብ ሱዳን የልዩ ልዩ ኃይሎች መረባረቢያ እየሆነች መምጣቷ ይታያል። ሻዕቢያ ከሱዳን አገዛዝ ጋር ያለው ግንኙነት እየተሻሻለ ሲሆን ወያኔ ደግሞ ምንም እንኳን ከሱዳን ጋር ወዳጅ ቢሆንም ከአሜሪካና ምዕራባውያን ጋር በመመሳጠር የደቡብ ሱዳንን መገንጠል እውን ለማድረግ እየሰራ መሆኑ ታውቋል። የደቡብ ሱዳን መገንጠል የምታቃወመው ግብጽም ቻይና ለኢትዮጵያና ሌሎች የአባይ ተፋሰስ ሀገሮች የግድብ ስራ እርዳታ እንዳትሰጥ ለቻይና አሳስባለች።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከተገኘው ዜና በሱማሌ ክልል የእስልምና ጉዳይ ጽ/ቤት ውስጥ ይሠሩ የነበሩ አምስት የአመራር አባላት ከ15 ቀን በላይ መታሰራቸው ታውቋል። የሱማሌ ክልል የእስልምና ጉዳይ ሊቀመንበር ም/ሊቀመንበርና ሌሎች የምክር ቤቱ አመራሮችም የታሰሩ ሲሆን የመታሰራቸው ምክንያት መንግሥትንና ዋናውን የእስልምና ጉዳይ ሃላፊን አንታዘዝም በማለታቸው እንደሆነ ተገልጿል።

ከእስልምና ጉዳዮችና ከክልሉ መንግሥት የመጣላቸውን መመሪያ አንቀበልም ያሉት እነዚሁ መሪዎች "እኛ ሃይማኖታዊ ጉዳይ እንጂ ፖለቲካዊ ጉዳይ ለመሥራት አይደለም እዚህ የተቀመጥነው" ማለታቸው ታውቋል።

በሌላ በኩል ለአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ለሊቀመንበርነት ታጭተው የነበሩት አንጋፋው የእስላም ምሁር ሐጂ በሽር  አሰራሩ አይስማማኝም በማለት ሃላፊነቱን ያልተቀበሉት መሆኑ ተገልጿል።  ም/ቤቱ ግን በጤና መታወክ ምክንያት አልፈልግም ብለዋል የሚል መልስ ሰጥቶ በምትካቸው ሌሎች ሰዎች እንዲቀመጡ አድርጓል።

"

በትግራይ ሽሬ የተለያዩ አካባቢዎች በ 1995 ዓ.ም. በተከሰተ በሽታ እስካሁን ከ250 እስከ 300 የሚደርሱ ሰዎች መሞታቸው ይፋ እየሆነ ነው፡፡ እስካሁን በተደረጉ ጥናቶች የበሽታው ምንነትን ማወቅ እንዳልተቻለ ይኸው ይፋዊ መግለጫ ያስረዳል፡፡ የበሽታ ምልክቶችም በአፍና በአፍንጫ የደም መፍሰስ፣ ከፍተኛ ትኩሳት፣ ትውከትና ተቅማጥ፣ የሰውነት መመናመን ናቸው፡፡ በበሽታው የተያዘ ሰው ከተያዘበት ጊዜ እስከ ስድስት ወር ባለው ጊዜ ህይወቱ እንደሚያልፍ መረዳት ተችሏል፡፡ ይህ እስከ ዛሬ የተደበቀ በሽታ ከሰው ወደ ሰው እንደማይተላለፍ የተነገረ ቢሆንም ይህን አመት ሙሉ በቁጥጥር ሥር ማዋል አለመቻሉ ከወያኔን ደንታ ቢስነት ባህርይ የመጣ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡

"

የመለሰ ዘናዊ ዘረኛ አገዛዝ በዚህ ሳምንትም በአስከፊ ፖለቲካው ቀጥሎበት ሕዝብን ሲያምስ ቆይቷል። የተከዜ ግድብ ተመረቀ፤ የጣና በለስ ቁፋሮው እየገፋ ነው፤ ወዘተ… ቢልም የመብራት ኃይል እጥረት ግን ይህ ነው በሚባል ደረጃ እንዳልተወገደ ነዋሪው ሁሉ የታዘበው ጉዳይ ነው።

**ወደ 7 ቢሊዮን ብር ውጪ እየጠየቀ ነው የተባለው የጣና በለስ ዕቅድ ባስልኮስት ወይም ሳሊኒ ኩባንያ ከመቀጠሉ በፊት የአውሮፓ ማህበር ከለገሰው ገንዘብ መለሰ ዜናዊ ፤ አዲሱ ለገሰና አያሌው ጎበዜ ድርሻቸውን ከጣሊያኑ የሳሊኒ ኩባንያ በጉቦ መልክ መውሰዳቸው ሊደበቅ አልቻለም።**

""

**መፈንቀል መንግስት ሊሞከርብኝ ነበር በሚል ሽፋን በቁጥጥር ባስገባቸው 27 ግለሰቦች ላይ የወያኔ ፍርድ ቤት የጥፋተኛነት ፍርድ ፈርዶባቸው የቅጣት ብያኔው ለመጪው ሳምንት ተላልፏል። ሞትና የዕድሜ ይፍታህ ቅጣትም ሊወሰን ይችላል የተባለ ሲሆን ባለው ሁኔታ ግን ወያኔ የሞት ፍርድ ላይበይን ይችላል የሚሉ ታዛቢዎች አሉ። ቀደም ሲል ከእስረኞቹ አንዱ ጡረታ የወጡት ጄኔራል አሳምነው ፅጌ በደረሰባቸው ድብደባ አንድ ዓይናቸው መጥፋቱን ቢገልጡትም ፍርድ ቤቱ ይህን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል። ጨካኞቹ የወያኔ ቅጥረኞች ድብደባ ሲያካሂዱ የአማራውን ሕዝብ እየሰደቡና እያዋረዱ እንደነበር ተጋልጧል። ወያኔ በትግራይ ጫካ እታገላለሁ ሲል በነበረበት ጊዜ ብዙ የአማራውን ሕዝብ የሚሰድቡ ዘፈኖች አስቀርጾ ያሰራጭ እንደነበርም የሚታወስ ነው። ይህ ዘረኛና አሳፋሪ ቡድን ከቀን ወደ ቀን በትግራይ ሕዝብና በቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ መሃል ቅራኔውን ለማስፋትና በዘረኛነት የተበከለ የትግራይ ወጣት ትውልድ ለመቅረጽ እየጣረ ነው።**